የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 18ኛ ዓመት ቁጥር 4<br>18th Year No. 4 | | ሀረር የካቲት 20 ቀን 2005<br>HARAR, Feb 27,2013 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 6.30<br>Unit Price Birr 6.30 | በሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖ.ሣ.ቁ. 952<br>P.O.Box 952 |


ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 112/2005 ዓ/ም

የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የሀብት ማስመዝገቢያ እና የጥቅም ግጭት ለማስወገድ የወጣ አዋጅ........ ገጽ 849

## አዋጅ ቁጥር 112/2005

## የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የሀብት ማስመዝገቢያ እና የጥቅም ግጭት ለማስወገድ የወጣ አዋጅ

ሀብትን ማሳወቅና ማስዝገብ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከልና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ፤

የመንግስት የስራ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይቀላቀል በየራሳቸው መንገድ የሚመሩበትን ግልጽ ሥርዓት መዘርጋት ሊፈጠር የሚችለውን የጥቅም ግጭት ለማስወገድ እንደሚረዳ በመታመኑ፤

በተሻሻለው የሀረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ሕገ-መንግስት አንቀጽ 51 (2) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሀብት ማስመዝገቢያ እና የጥቅም ግጭት ማስወገጃ አዋጅ ቁጥር 112/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ሀብት" ማለት ማንኛውም የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ንብረት ሲሆን የመሬት ይዞታንና ዕዳን ይጨምራል፡፡
2. "መንግስት" ማለት የሀረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ማለት ነው፡፡

3. "ክልል ምክር ቤት" ማለት የሀረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት የሕዝብ ተመራጮች ምክር ቤት ማለት ነው፡፡
4. "ክልል መስተዳድር ምክር ቤት" ማለት የሀረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት የክልል አስፈጻሚው አካላት ምክር ቤት ማለት ነው፡፡
5. "ኮሚሽን" ማለት የሀረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማለት ነው፡፡
6. "የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት" ማለት የሀረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት የታችኛው እርከን ተመራጮች ምክር ቤት ማለት ነው፡፡
7. "የቀበሌ መስተዳድር ጽህፈት ቤት" ማለት የሀረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት የታችኛው እርከን የአስፈፃሚው አካል ጽህፈት ቤት ማለት ነው፡፡
8. "የመንግስት መሥሪያ ቤት" ማለት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በጀት የሚተዳደርና የክልሉ የመንግስት ስራ የሚከናወንበት ማለት ነው፡፡
9. "የመንግሥት የልማት ድርጅት" ማለት በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት ተቋቁሞ የምርት፣ ስርጭት፣ ግንባታ እና አገልግሎት ሰጪ ወይም ከኢኮኖሚ ልማትና ከሌሎች የንግድ ስራዎች ጋር በተያያዘ የተሠማራ ማለት ነው፡፡
10. "የሥነ ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም የሥነ-ምግባር ኦፊሰር" ማለት በመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት የሥነ ምግባር ማስፋፋትና ክትትል ሥራዎችን የሚያስተባብርና የሚያማክር ሙስናንና ብልሹ አሰራሮችን የሚከላከል አካል ነው፡፡
11. "ተሿሚ" ማለት የሚከተሉትን ይመለከታል፡-
   ሀ. የክልሉ መንግሥት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ቢሮ ኃላፊዎች፣ ምክትል ቢሮ ኃላፊዎችና በእነዚሁ ደረጃ የሚገኙ ማንኛውም የክልሉ መንግስት ኃላፊዎችን እና ዋና ኦዲተር፣
   ለ. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ፣ ም/ፕሬዚዳንት እና ዳኞችን፣ እንዲሁም የከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች ዳኞችና ቃዲዎች፣
   ሐ. የከተማ ከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ ተሿሚ እና ሌሎች የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች፣
   መ. ኮሚሽን፣ ባለስልጣን፣ ጽህፈት ቤት፣ ኤጀንሲ እና የመሳሰሉ የክልሉ መንግሥት አካላት ኃላፊዎችንና ምክትሎቻቸውንም፣
   ሠ. የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪ እና የቀበሌ መስተዳድር አስተባባሪዎችን፣
   ረ. በክልሉ መንግስት የሚተዳደሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዲን፣ ም/ዲን፣ ሥራ አስኪያጅ እና ም/ሥራ አስኪያጅን፣
   ሰ. የመንግስት የልማት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ አባል፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ወይም ምክትል ሥራ አስኪያጅ በመሆን የተሾሙትን ወይም የተመደቡትን ፣ ወይም የተቀጠሩትን ያካትታል ፡፡

12. "ተመራጭ" ማለት የሚከተሉትን ያካትታል፡፡
   ሀ. የሀረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ምክር ቤት አባላትን፣
   ለ. የቀበሌ አስተዳድር ምክር ቤት አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤን፡፡
13. "የመንግስት ሠራተኛ" ማለት በመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት የሚሠሩ የሚከተሉትን ሠራተኞችን ያጠቃልላል፡-
   ሀ. በሥራ ሂደት ሃላፊነት፣ በዳይሬክተርነት አገልግሎት ኃላፊነት እና ከዚያ በላይ ባሉት እና ከዚህ ጋር በተመጣጣኝ ደረጃ የሚገኙ፣
   ለ. የተሿሚዎች አማካሪ፣
   ሐ. ውሳኔ የመስጠት ወይም የማስፈጸም፣ ፈቃድ የመስጠት፣ የመቆጣጣር፣ ገቢ የመወሰን ወይም የመሰብሰብ፣ ግዥን የመወሰን ወይም የማስፈጸም፣ የመሬት አስተዳደር ሥራን የሚያከናውኑ ሰራተኞችን ፣ ዓቃቢያነ-ሕግ፣ የሕግ ኦፊሰሮች፣ የሕግ አማካሪዎ ፣ ነገረ-ፈጆች፣ መርማሪዎች፣ ትራፊኮች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ወይም የንግድ ተቆጣጣሪዎች፣ መሃንዲሶች እና፣
   መ. ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ተለይተው የሚወሰኑ ሌሎች በመንግስት መሥሪያ ቤት እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚገኙ ሠራተኞችን ይጨምራል፡፡
14. "ቤተሰብ" ማለት የተሿሚው፣ የተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛው ሚስት ወይም ባል ወይም በሥሩ የሚተዳደሩ ዕድሚያቸው አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸው ልጆች ሲሆን ጋብቻ ሣይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የሚኖሩ እና የጉዲፈቻ ልጅን ይጨምራል፡፡
15. «የቅርብ ዘመድ» ማለት የተሿሚው፣ የተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛው ወላጅን፣ ተወላጅን፣ እህትን፣ ወንድምን እና ሌሎች እስከ ሦስተኛ ደረጃ የሚገኙትን የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡
16. «ሰው» ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>
   1. ይህ አዋጅ በክልል መንግስት፣ በከተማ አስተዳደር እና በቀለቤ በሚገኙ በማንኛውም ተመራጭ፣ ተሿሚ እና መንግስት ሰራተኞች እንዲሁም በክልሉ የመንግስት የልማት ድርጅት ተሿሚዎችና ሰራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል ፡፡
   2. በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ያካትታል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ሀብትን ስለማሳወቅና ስለማስመዝገብ</u>

4. <u>የማስመዝገብ ግዴታ</u>
   1. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ፡-
      ሀ. በራሱ ወይም በቤተሰቡ ባለቤትነት ወይም ይዞታው ሥር የሚገኝ ሀብትን እና፣
      ለ. የራሱንና የቤተሰቡን የገቢ ምንጭ የማሳወቅና የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሀብቱን የሚያስመዘግብ ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የራሱንና የቤተሰቡን ሀብትና የገቢ ምንጭ ለየብቻ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ቅጽ ላይ በመሙላት ትክክለኛነቱንም በፊርማው ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 5. <u>በምዝገባ ስለማይካተት ሀብት</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቢኖርም የሚከተሉት ሀብቶች አይመዘገቡም፡-
   ሀ. በውርስ ተግኝቶ በጋራ የተያዘና ለወራሾቹ የግል አገልግሎት የሚውል ንብረት፣
   ለ. የቤት እቃዎችና የግል መገልገያዎች፣
   ሐ. ከጡረታ የሚገኝ ገቢ፡፡
2. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) መሠረት በጋራ የተያዘ ንብረት በወራሾች መካከል እንደተከፋፈለ ድርሻውን አሳውቆ ማስመዝገብ አለበት፡፡

## 6. <u>ስለመዝጋቢ አካል</u>

1. የተሿሚ ፣ የተመራጭንና የመንግስት ሠራተኛን ሀብት የሚመዘግበው ኮሚሽኑ ይሆናል፡፡
2. ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተሿሚን፣ ተመራጭን ወይም የመንግስት ሠራተኛን ሀብት እንዲመዘግብ እንደሁኔታው በሙሉ ወይም በከፊል የሥነ-ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም ኦፊሰርን ሊወክል ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ውክልና የተሠጠው የሥነ ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም ኦፊሰር በዚህ አዋጅ አንቀጽ (4) ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቀረበለትን የሀብት ማስመዝገቢያ ሰነድ ምዝገባው በተደረገ በ30 ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ያስተላልፋል፡፡
4. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተከናወኑ የሀብት ምዝገባ ሠነዶች ያስቀምጣል፣ ይጠብቃል፡፡ ሀብቱን ላስመዘገበ ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የምዝገባ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሠጣል፡፡

## 7. <u>ምዝገባ ስለሚካሄድበት ጊዜ</u>

1. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለበት ከስድስት ወራት በኋላ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ሀብቱን ማሳወቅና ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. ማንኛውም አዲስ ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ሀብቱን የሚያሳውቀውና የሚያስመዘግበው ከተሾመበት፣ ከተመረጠበት ወይም ከተቀጠረበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት ሀብቱን ያስመዘገበው ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ከዚያ በኋላ ሀብቱን የሚያሳውቀውና የሚያስመዘግበው በየሁለት ዓመቱ ሆኖ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ30 ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

8. **የምዝገባ ጊዜን ስለማራዘም**

1. የምዝገባ ጊዜ እንዲራዘምለት የሚጠይቅ ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ምዝገባውን ማራዘም ያስፈለገበትን በቂ ምክንያት በጽሁፍ በመግለፅ የምዝገባ ጊዜው በተጠናቀቀ በ5 ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ለሚመለከተው የሥነ ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም ኦፊሰር ማመልከት ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም ኦፊሰር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የቀረበለት ጥያቄ በበቂ ምክንያት የተደገፈ ሆኖ ሲያገኘው የምዝገባውን ጊዜ ለአንድ ጊዜ እስከ 30 ቀናት ሊያራዝም ይችላል፡፡
3. የምዝገባ ጊዜ እንዲራዘምለት ለሥነ-ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም ኦፊሰር ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ የተደረገበት አመልካች ውሳኔው በደረሰው በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለኮሚሽኑ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ኮሚሽኑ የሚሠጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

9. **ዘግይቶ ስለማስመዝገብ**

በመደበኛው ወይም በተራዘመለት የማስመዝገቢያ ጊዜ ውስጥ ሀብቱን ያላስመዘገበ ተሿሚ ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ብር 1000 መቀጫ ከፍሎ በ30 ቀናት ውስጥ ማስመዝገብ አለበት፡፡

10. **ከስንብት በኋላ ስለሚኖሩ ግዴታዎች**

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በጡረታ ሲገለል ወይም በማንኛውም ምክንያት አገልግሎቱን ሲያቋርጥ ሀብቱን በ30 ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ለሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም የስነ-ምግባር እንዲሁም ከሁለት ዓመት በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

11. **የምዝገባን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ**

1. ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ (4) ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም በመንግስት ሠራተኛ በተሞላ መረጃ ያልተሟላ፣ ትክክል ያልሆነ ወይም የሀሰት መረጃ የያዘ መሆኑን ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖረው ወይም ሀብቱ በትክክል አልተመዘገበም የሚል ጥቆማ ሲቀርብ ወይም በተፈጸመ ወንጀል ምክንያት ምርመራ ሲጀምር የምዝገባውን ትክክለኛነት የማጣራት ተግባር ያከናውናል፡፡
2. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) መሠረት የማጣራት ተግባር ሲያከናውን፡-
   ሀ. ጉዳዩ የሚመለከተው ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ተጨማሪ መረጃ ወይም ማብራሪያ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው፣
   ለ. የተሿሚውን፣ የተመራጩን ወይም የመንግሥት ሠራተኛውን ሀብት የሚመለከት መረጃ ያለው ባንክ፣ የፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው መረጃውን እንዲሰጥ ሊያዘው፣ እና
   ሐ. የዋና ኦዲተርን ወይም የሌላ አግባብነት ያለውን አካል ሙያዊ ድጋፍ ሊጠቀም ይችላል፡፡

3. ኮሚሽኑ ያልተሟላ፣ ትክክል ያልሆነ ወይም የሀሰት መረጃ መቅረቡን በማስረጃ ሲያረጋግጥ ጥፋት በፈጸመው ሰው ላይ በህጉ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድበት ያደርጋል፡፡

12. የምዝገባ መረጃ ተደራሽነት

1. በኮሚሽኑ እጅ የሚገኝ ማንኛውም የተሿሚ፣ የተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የሀብት ምዝገባ መረጃ ለህዝብ ክፍት ይሆናል፡፡
2. ስለሀብት ምዝገባ መረጃ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ጥያቄውን በጽሁፍ ለኮሚሽኑ ወይም ጉዳዩ ለሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም ስነ-ምግባር ኦፊሰር ሊያቀርብ ይችላል፡፡
3. ኮሚሽኑ ወይም የሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም ኦፊሰር ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል የምዝገባውን መረጃ ለጠየቀው ሰው መስጠት አለበት፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የቤተሰብ ሀብትን የሚመለከት የምዝገባ መረጃ ለፍትህ ሥራ ወይም ኮሚሽኑ አስፈላጊ ነው ብሎ ለሚወስነው ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በሚስጥር የሚያዝ ይሆናል፡፡
5. ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በየሁለት ዓመቱ ስላከናወነው የሀብት ምዝገባ አጠቃላይ መረጃ በሪፖርት መልክ ያወጣል፡፡

13. የሀብት አለመመዝገብ የሚያስከትለው ውጤት

በዚህ አዋጅ መሠረት ያልተመዘገበ ማናቸውም የተሿሚ፣ የተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ሀብት ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 419 (2) ድንጋጌ አፈጻጸም ሲባል ምንጩ እንዳልታወቀ ንብረት ይቆጠራል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የጥቅም ግጭትን ስለማሳወቅና ስለማስወገድ

14. መርህ

1. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የያዘውን መንግሥታዊ የሃላፊነት ቦታ የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ ማዋል አለበት፡፡ በማንኛውም ምክንያት ቢሆን በሥራው አጋጣሚ ያገኘውንና ሕዝብ እንዲያውቀው ያልተደረገን መረጃ ለግል ጥቅሙ ማዋል የለበትም፡፡
2. በዚህ ክፍል የተደነገጉት ድንጋጌዎች የመንግስት መስሪያ ቤቱን ወይም የመንግስት ልማት ድርጅቱን የውስጥም ሆነ የውጭ አገልግሎት ያጠቃልላል፤
2. በአንቀጽ 2 ንዑስ ቁጥር 13 ከተመለከቱት ሠራተኞች በተጨማሪ ማንኛውንም የመንግስት መስሪያ ቤቱን ወይም የመንግስት ልማት ድርጅቱ ከሚሰጣቸው አገልግሎት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሠራተኞች በአጠቃላይ ይሸፍናል፡፡

15. ስጦታ፣ መስተንግዶና የጉዞ ግብዣ

1. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የመወሰን ሥልጣኑን የሚፈታተን ወይም የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ መቀበል የለበትም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የቀረበለትን ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ያለመቀበል በስራ ግንኙነት ላይ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ስጦታውን፣ መስተንግዶውን ወይም የጉዞ ግብዣውን ለመቀበል ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የተቀበለው ስጦታ አግባብ ላለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ገቢ ማድረግ ወይም የጉዞ ግብዣውን ለኮሚሽኑ ወይም አግባብ ላለው የሥነ-ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም ኦፊሰር ማሳወቅ አለበት፡፡

## 16. የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ መወሰድ ስላለበት እርምጃ

1. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በመንግስት የሥራ ሃላፊነቱና በራሱ ወይም በቅርብ ዘመዱ የግል ጥቅም መካከል ግጭት ሊያስከትልበት የሚችል ጉዳይ ሲያጋጥመው፡-
   ሀ. በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ወይም አስተያየት ከመስጠት እንዲሁም ከኃላፊነቱ ጋር የማይጣጣም ወይም ታማኝነቱን ጥርጣሬ ውስጥ የሚጥል ማንኛውንም ድርጊት ከመፈጸም መቆጠብ እና
   ለ. ሁኔታውን ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የጥቅም ግጭት ሊከሰት መቻሉ የተገለጸለት የበላይ ኃላፊ እንደሁኔታው ተሿሚው፣ ተመራጩ ወይም የመንግሥት ሠራተኛው ጉዳዩን ማየቱን እንዲቀጥል መመሪያ ሊሰጠው ወይም ሌላ ሰው ተተክቶ እንዲያየው ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 17. የጥቅም ግጭት መከሰቱን ተከትሎ ስለሚወሰድ እርምጃ

ማንኛውም ተሿሚ ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት የሥራ ኃላፊነቱና በራሱ ወይም በቅርብ ዘመዱ የግል ጥቅም መካከል ግጭት መከሰቱን ተከትሎ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በበላይ ኃላፊው ሲጠየቅ ጥፋተኛ መሆኑን በይፋ አምኖ ይቅርታ የመጠየቅ ወይም ራሱን ከኃላፊነት የማግለል ግዴታ አለበት፡፡

## 18. ከሥራ መልቀቅ በኋላ ስለሚኖር ክልከላ

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ሥራ በለቀቀ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ሲቆጣጠራቸው ከነበረው ሰዎች ጋር ጥቅም የሚያስገኙ ሥራዎች መሥራት የለበትም፡፡ ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 19. የጥቅም ግጭትን የማሳወቅ ግዴታን ስላለመወጣት

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የጥቅም ግጭት መኖሩን የማሳወቅ ግዴታ ያለበት በዚህ አዋጅ መሠረት የማሳወቅ ግዴታውን ካልተወጣ አግባብ ባለው የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግሥት ልማት ድርጅት የሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ህግ ወይም ደንብ ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 20. ጥቆማ ስለማቅረብ

1. ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ጥሷል በሚለው ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ላይ ጥቆማ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ጥቆማው እስከተቻለ ድረስ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር በጽሁፍ ለኮሚሽኑ ወይም አግባብ ላለው የሥነ-ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም ኦፊሰር ይቀርባል፡፡
3. በቀረበው ጥቆማ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የምርመራ ሂደቱና መዛግብቱ በሚስጥር ተይዘው ይቆያሉ፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት በቀረበ ጥቆማ የተገኘው መረጃ በወንጀል ህግ አንቀጽ 419(2) መሰረት የሀብት መወረስ ዉሳኔ ለማሰጠት ካስቻለ የተወረሰው ሀብት ከሚያስገኘው ገቢ ውስጥ 25 በመቶ ለጠቋሚው ይከፈላል፡፡

### 21. የአዋጁን ተፈጻሚነት ስለማረጋገጥ

ማንኛውም የመንግሥት መስሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት እና የበላይ ኃላፊዎቻቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ፡-

1. ተሿሚዎች፣ ተመራጮችና የመንግሥት ሠራተኞች ሀብታቸውን በወቅቱ እንዲያስመዘግቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡
2. አግባብ ያላቸው የሥነ-ምግባር ደንቦችን አውጥቶ ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡

### 22. ቅጣት

1. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ፡-
   ሀ. ሀብቱን በዚህ አዋጅ መሠረት ለምዝገባ ሳያሳውቅ ከቀረ ወይም ሆን ብሎ ትክክል ያልሆነ መረጃ ከሰጠ ፣ ወይም
   ለ. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ከተቀበለ ወይም የተቀበለውን ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ሳያሳውቅ ከቀረ፣ በወንጀል ህግ አንቀጽ 417 ወይም/እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል፡፡
2. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በማንኛውም ሰው ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 መሠረት ለኮሚሽኑ ወይም ለሥነ-ምግባር መከታተያ ቡድን ወይም ኦፊሰር ጥቆማ አቅርቧል ወይም ምስክርነት ሰጥቷል ወይም ለሥነ-ምግባር ኦፊሰር ጥቆማ ለማቅረብ ወይም ምስክርነት ለመስጠት ተዘጋጅቷል በሚል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የበቀል እርምጃ የወሰደ እንደሆነ በወንጀል ህግ አንቀጽ 444 ወይም እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ይቀጣል፡፡
3. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ኃላፊ ስራ አስኪያጅ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ላይ በተደነገገው መሰረት አስፈላጊውን ድጋፍ ለኮሚሽኑ ሳያደርግ ቀርቶ በዚህም ምክንያት በህዝብና መንግስት ጥቅሞች ላይ ጉዳት ከደረሰ በወንጀል ህግ አንቀጽ 420 እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ይቀጣል ፡፡

4. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የጥቅም ግጭት መኖሩን ሳያሳውቅም ሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16(2) መሠረት ተፈቅዶለት ሲሠራ የመንግሥት ኃላፊነቱን ተጠቅሞ የራሱን ወይም የቅርብ ዘመዱን የግል ጥቅም ያራመደ እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል፡፡
5. ማንኛውም ሰው በክፉ ልቦና በመነሳሳት ምንም ዓይነት መሠረት የሌለው ጥቆማ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 መሠረት ካቀረበ እስከ ሦስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራት ወይም እስከ ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) የሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

23. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ህግ ወይም ማንኛውም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

24. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

1. ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

25. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት 30 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሀረር የካቲት 20 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ሙራድ አብዱልሃዲ**

**የሀረሪ ሕዝብ ክልል መንግሥት**

**ፕሬዚዳንት**